ግልፅ ደብዳቤ
ለወ/ሮ ትዝታ በላቸው
በአሜሪካን ድምፅ ሬዲዮ የአማርኛው ክፍል ባልደረባ

<u>ዋሽንግተን ዲሲ</u>

ጉዳዩ የቃለ ምልልስ ቅጂዎችን ስለመጠየቅ

ሰሞኑን ከእርስዎ ጋር ያደረግኋቸው ሁለት ቃለ ምልልሶች ለአራት የተለያዩ ቀናቶች ተከፋፍለውና መጠናቸው በግማሽ እንዲያጥር ተደርገው በሬዲዮ ጣቢያው መተላለፋቸውን በአንክሮ ተከታትያለሁ፡፡ ከቃለ ምልልሱ መተላለፍ በኋላ በሕዝብ አስተያየት ስም በእኔ ላይ እየቀረበ ያለው የፈጠራና የአሉባልታ ክስ ተገቢ አለመሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሰጠኋቸው እነዚህ ቃለ ምልልሶች በተሟላ ይዞታቸው ሳይሆን እኔን ሊጎዳ በሚችል ደረጃ፤ በጥንቃቄ ቅድመ ምርመራ ተደርጎባቸውና ብዙ ጠቃሚ ሃሳቦች ተቆርጠው ሚዛናዊ ባልሆነ ሁኔታ እንዲቀርቡ መደረጋቸውን አድምጫለሁ፡፡ በተጨማሪም በፕሮግራሙ ውስጥ በአጋጣሚ ሾልከው በመግባት እኔን በመደገፍ የቀረቡ ጥያቄዎችና ለጥያቄዎቹ የተሰጡ መልሶች እንዲሁም እውነቱን ሊያስረዱ የሚችሉ በርካታ ጥያቄና መልሶች ሙሉ በሙሉ ተቆርጠው እንዲወጡ መደረጋቸውን ለማወቅ ችያለሁ፡፡
የዴሞክራሲ አርአያና ምሳሌ በሆነ አገር ሬዲዮ ጣቢያ ላይ እንዲህ ዓይነት የሙያ ሥነ ምግባርን ያልተከተለና የሃሳብ ነፃነትን የሚፃረር ፕሮግራም ሲሰራ በማየቴ የተሰማኝን ከፍተኛ ቅሬታ እየገለፅኩ በእራሴ መንገድ አድማጩ ሕዝብ የተሟላውን የቃለ ምልልስ ይዘት እንዲያዳምጠው ለማድረግ ስለምፈልግ ከእርሶ ጋር ያደረግኋቸው ሁለት ቃለ ምልልሶች ያልተቆራረጡ የተሟሉ ቅጂዎች በተቻለ ፍጥነት እንዲልኩልኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

ፊርማ የማይነበብ
ልደቱ አያሌው
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልና
የኢዴፓ ፕሬዚዳንት

ግልባጭ
- ለአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ የአማርኛው ክፍል፤
- ለኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲ ፓርቲ (ኢዴፓ)፤
- በኢትዮጵያ ለአሜሪካ መንግሥት ኤምባሲ፤
- ለሁሉም የአገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን